

## ብቸኛውና እውነተኛው እግዚአብሔር በእርግጥ ማን ስለመሆኑ ተደንቃችሁ ታውቃላችሁ?

ብቸኛውና እውነተኛው እግዚአብሔር መንፈስ ነው። እንደእኔና እንደ እናንተ የሚጨበጥና የሚታይ አካል የለውም። ልታዩት ባትችሉም እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ይገኛል። ልጆች! እግዚአብሔር ሁልጊዜም ያያችኋል፤ ይሰማችኋል፤ ሁልጊዜም የምታደርጉትን ነገር ያውቃል።

እግዚአብሔር ፍጹም እንደሰዎች መማር የለበትም። ብዙ ነገር ያው ቃሉ ከሚባሉ ሴቶችና ወንዶች ይልቅ የበለጠ ብዙ ነገር ያውቃል።

ዓለምንና በውስጧ ያሉትን ተራሮች፣ ዛፎች፣ ወፎችንና እንስሳትን ሁሉ የፈጠረው እርሱ ነው። እኔንና እናንተንም እኮ የፈጠረን እግዚአብሔር ነው። እንዲያውም እኔና እናንተ የእርሱ ልዩ ፍጥረቶች ነን።

እግዚአብሔር ኃያል ስለሆነ ሁሉንም ነገር ማድረግ ይችላል። ማንኛውንም ነገር መስራት ይችላል። እግዚአብሔርን የሚያቅተው ነገር የለም። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። ማለትም እንከን የሌለውና ትክክል ነው። እርሱ ጥሩ ስለሆነ ጥሩ ያልሆነውን ነገር በፍጹም አያደርግም።

እግዚአብሔር በፍጹም አይለወጥም። እርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ህያው ሆኖ ሳይለወጥ ይኖራል። እግዚአብሔር ደግሞ መንግስተ ሰማይ የተባለ ያማረ ስፍራን አዘጋጅቶልናል። መንግስተ ሰማይ ትክክልና ጥሩ ነገር ስላለበት በጣም ያምራል። እግዚአብሔር ስለሚወዳችሁ በዚያ በሚያምረው መንግስተ ሰማይ ከእርሱ ጋር አብራችሁ እንድትኖሩም ይፈልጋል። የእግዚአብሔር ሀሳብና ፍላጎት ታዲያ ተጽፎ የሚገኝበት ቃሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይባላል።

*«...እኔ አምላክ ነኝና፣ ሌላም የለምና... እንደእኔም ያለ ማንም የለም።» (ኢሳ. 46፥9)*







## መጽሐፍ ቅዱስ ምን ዓይነት መጽሐፍ እንደሆነ አስደንቋችሁ ያውቃል?

«ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው ማነው? ትክክለኛና እውነተኛ መሆኑንስ እንዴት ማረጋገጥ እንችላለን» ብላችሁ ትደነቁ ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር የተሰጠ እጅግ ልዩ የሆነ መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ሲሆን በውስጡ ያለው ቃል ሁሉ ደግሞ እውነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለእኛ ለሰዎች ያለውን እቅድ ስለሚናገር በጣም አስፈላጊ መጽሐፍ ነው። ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መጽሐፍ መሆኑን በምን እናውቀለን? መጽሐፍ ቅዱስ በ1600 ዓመታት ውስጥ እግዚአብሔር ለ40 የተለያዩ ሰዎች ተናግሯቸው የጻፉት መጽሐፍ ነው። የጻፉት ሰዎች ምን መጻፍ እንዳለባቸውና እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው ሁሉ የመራቸው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለእነዚህ ሰዎች የነገራቸው ጮኽ ብሎ በጆሮአቸው እንዲሰሙት ይሆን ወይም ደግሞ በጸጥታ ወደ አእምሮአቸው ያምጣ አናውቅም።

እግዚአብሔር ለሰዎች ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች ነግሯቸው ጽፈዋል። ከእነዚህም ነገሮች ውስጥ ብዙዎች ተፈጽመዋል። ገና ያልተፈጸሙና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉት ነገሮችም ወደፊት ይፈጸማሉ።

በሌላ ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 66 መጽሐፍት አሉ። እነኚህ መጽሐፍት ሁሉ እንኳን ይስማማሉ፤ ይገጣጠማሉ። ይህንንም ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለዚህም እኔና እናንተ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ቅዱሳን መጽሐፍት ሁሉ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን መልእክቶች መሆናቸውን እርግጠኛ መሆን እንችላለን። ሌላው ቀርቶ እያንዳንዷ ቃል እንኳ የእግዚአብሔር ናት። በምድር ላይ የምናያቸው ነገሮች ሁሉ ለዘለዓለም አይኖሩም፤ ይለወጣሉ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ለዘላለም ይኖራል።

*«የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ......» (2 ጢሞ. 3፥16)*






## ልታስቡበት የሚገባ ነገር

ዓለምንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ የፈጠረው ማን ነው?

ከቁጥሮቹ ስር ያሉትን ነጠብጣቦች በማገናኘት እግዚአብሔር እኛን የሚናገርበትን አንደኛውን መንገድ ታገኙታላችሁ።




# የእግዚአብሔር መጽሀፍ

## የዕለቱ ጸሎት፦

እግዚአብሔር ሆይ መጽሐፍህን በደበልጥ እንዳጠና እርዳኝ።


# ስለዓለም አስደናቂ አጀማመር አስባችሁ ታውቃላችሁ?

ለመሆኑ ዓለም ከየት ተገኘች? ዓለምና በውስጧ ያሉት በድንገት የሆኑ (የተከሰቱ) ናቸው? ሰዎች ከየት ነው የመጡት? ልጆች! መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ ይነግረናል። በዘፍ. 1፥1 ላይ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።» ይላል። እግዚአብሔር ሰማይን፣ ከዋክብትን፣ ፀሐይን ፈጠረ። እንደዚሁም የምንኖርባትን ክብና ትልቅ ዓለም፣ በውስጧ ያሉትን ውቅያኖሶች፣ ተራሮችና ዛፎች ፈጠረ፤ ከዚያም በኋላም ደግሞ እንስሳትን ፈጠረ። እግዚአብሔር ግን እንዴት ያለ ኃይል ነው!

እግዚአብሔር ውብ ምድር ካበጀ በኋላ አንድን ሰው ፈጠረ። ያንንም ሰው የፈጠረው ከምድር አፈር ሲሆን የህይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት። ሰውም ለዘላለም ህያው ነፍስ ያለው ሆነ። ምንም እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ቢሆንም ሰውን በአምሳሉ ፈጠረው። ስም አወጣላት። አዳም ግን ብቸኛ ነበረ። አዳም እንደ እርሱ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ጓደኛና ረዳት ያስፈልገው ነበር። እግዚአብሔር አንድ ቀን አዳምን ከባድ እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገና ከጎኑ አጥንትን ወሰደ። ከዚህ አጥንትም እግዚአብሔር የመጀመሪያዋን ሴት ፈጠረ። አዳም ከእንቅልፉ ሲነቃ ይህችን ሴት ሚስቱ አድርጎ ሰጠው። ይህች ሴት ሄዋን ነበረች። አዳምና ሄዋን ይኖሩበት የነበረው ቦታ ውብ የአትክልት ስፍራ ነበር። እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ በጣም ጥሩ ነበር። እግዚአብሔር ታላቅና ብልኅ ፈጣሪ ነው።

*«አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ፤ ሰማያት ሰማዩን ሠራዊታቸውንም ሁሉ፣ ምድርንና በእርስዋ ያሉትን ሁሉ፣ ባህሮችንና በእነርሱ ውስጥ ያለውን ሁሉ ፈጥረሃል፣ ሁሉንም ህያው አድርገኸዋል» (ነህ 9፥6)*







## በዓለም ላይ ለምን በጣም ከፍተኛ መከራ እንዳለ ተደንቃችሁ ታውቃላችሁ?

ልጆች! አንዳንድ ጊዜ «በዓለም ላይ የሚያሳዝን ነገር ይህን ያህል ለምን ይኖራል?» ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል። ሰዎች ለምን ይታመማሉ? እርስ በእርሳቸውስ ለምን ይጣላሉ? ለምን ጦርነት ይፈጥራሉ? እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር ሁሉ ነገር መልካምና ውብ ነበር። ነገር ግን በዓለም ላይ የነበሩት መልካምና ውብ ነገሮች ብዙ ጊዜ አልቆየም፤ አሁንም የሉም። ሕመም፣ ሐዘን፣ ጦርነትና መገዳደል በዓለም በብዛት ይታያል። ነገሮች ለምን እንደዚህ ተበላሹ? ልጆች! ለዚህ ምክንያቱ ሰዎች ለእግዚአብሔር ህግ አለመታዘዛቸው ነው። ሰዎች ኃጢአትን በመስራት የእግዚአብሔርን መልካም ፍጥረት ሁሉ አበለሻሹት።

እግዚአብሔር አዳምንና ሄዋንን ባማረው የአትክልት ስፍራ ሲያኖራቸው አንድን ዛፍ አሳይቷቸው «ከዚህ የዛፍ ፍሬ እንዳትበሉ፤ ከበላችሁ ግን ትሞታላችሁ» ብሎ ነገራቸው።





አንድ ቀን ግን የእግዚአብሔር ጠላት የሆነው ሰይጣን ሄዋንን አሳሳታትና ከዚያ የዛፍ ፍሬ በላች፤ አዳምም ደግሞ በላ።

እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ባለመፍቀዳቸው ምክንያት ሁለቱም ሰዎች ኃጢአትን አደረጉ። እግዚአብሔርም ኃጢአትን በመስራታቸው አዳምና ሄዋን የአትክልት ስፍራውን ለቅቀው እንዲወጡ አደረገ። ምድርም እሾኽንና አሜካላን እንደምታበቅል፤ እነ አዳምም መድከም፣ መታመምና የሥጋን ሞት እንደሚገባቸው ተነገራቸው። ልጆች! የኃጢአት ዋነኛውና በጣም መጥፎ የሆነው ውጤቱ አዳምንና ሄዋንን ከቅዱሳን ንጹህ ከሆነው እግዚአብሔር መለየቱ ነው። ከዚያ በኋላ የሚወለደው ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ሆኖና ከእግዚአብሔር ተለያይቶ ይሄድ ጀመር። እግዚአብሔር ግን አዳምንና ሄዋንን ይወዳቸው ነበር።

በአንድ ወቅት አዳኝ እንደሚመጣ ዓለምንም ከኃጢአት ቅጣት እንደሚያድንና እኛን መልሶ ከእግዚአብሔር እንደሚያስታርቀን ቃል ገባላቸው።

*«ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ፤ በኃጢአትም ሞት፣ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ» (ሮሜ 5፥12)*

## ሊታሰቡበት የሚገባ ነገር


እግዚአብሔር እጅግ ኃያል ነው። እርሱ ብቻውን ዓለምንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ ፈጠረ።



## የዕለቱ ጸሎት፦

ልጆች! እግዚአብሔርን ስለድንቅ ፍጥረቱ አመስግኑት። ማንነቱንም በደንብ ማወቅ እንድትችሉ ወይም እርሱነቱ በደንብ እንዲገልጽላችሁ ጠይቁት።





## ኃጢአትን ለምን እንደምትፈጽሙ የመደነቅ ሐሳብ አድሮባችሁ ያውቃል?

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ነገር ማድረግ እንዳለባቸው እያወቁ ነገር ግን ትክክለኛ ያልሆነውንና የተሳሳተውን ነገር ለምን እንደሚያደርጉ ግራ ይገባቸዋል። ለመሆኑ እኔና እናንተ ኃጢአትን እንድንወድ የሚያደርገን ምንድነው? እግዚአብሔር ሁልጊዜም ሊከተሉት ለሚፈልጉ ሰዎች መመሪያና ህግ አለው። ነገር ግን ገና ድሮ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች የእግዚአብሔርን የመጀመሪያ ህግ ጣሱ። ያኔ አዳምና ሄዋን ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ ኃጢአትን ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ፤ ሰው ሁሉ ሲወለድ ኃጢአትን ከመፈለግ ጋር ነው የሚወለደው። የአዳምና የሄዋን ልጆች የተወለዱት ኃጢአተኞች ሆነው ነበር፤ እኔና እናንተም ስንወለድ ልክ እንደ እነርሱ ታጢአትን ከመፈለግ ጋር ነው የተወለድነው።


ለመሆኑ ኃጢአት ምንድነው? ኃጢአት የሚባለው የእግዚአብሔርን ህግ የሚያፈርስ ነገርን ማሰብ፣ መናገር ወይንም ማድረግ ነው።

መጽሀፍ ቅዱስ በሮሜ 3፥23 ላይ «ሁሉ ኃጢአትን ሰርተዋልና የእግዚ. አብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል» ይላል። እንደ እግዚአብሔር ጻድቅ የሆነ ማንም የለም። ልጆች! መጥፎ ነገሮችን እንድታደርጉ፣ እንድትዋሹ፣ እንድትጣሉ ወይም ደግሞ ስለሌላ ሰው ጥሩ ያልሆነ ነገር እንድታስቡ የሚያደርጋችሁ በልባችሁ ያለው ኃጢአት ነው። ከዚህ ኃጢአት ደግሞ በራሳችሁ ጥረት ማምለጥ አትችሉም። ኃጢአታችሁን ይቅር ሊልና ከእናንተም ሊያስወግደው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ኃጢአታችሁ ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚያራርቃችሁ የእግዚአብሔርን የኃጢአት ይቅርታ መቀበላችሁ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ይህ ኃጢአታችሁ ይቅር ካልተባለላችሁና ነጻ ካልወጣችሁ በቀር አንድ ቀን ለዘላለም ከእግዚአብሔር ትለዩና ለኃጢአተኞች ወደ ተዘጋጀው ከባድ የቅጣት ቦታ ትጣላላችሁ።

*«... ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች....» (ኢሳ. 59፥2)*








## እግዚአብሔር ኃጢአትን መቅጣት ያለበት ለምን እንደሆነ ተደንቃችሁ ታውቃላችሁ?

ኃጢአት እንደዚህ የከፋ ነገር የሆነው ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። ይህም ማለት በእርሱ ዘንድ ምንም እንከን የለም፤ እርሱ መልካም ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ በመሆኑ ምክንያት ኃጢአትን ስንሰራ ሳይቀጣን እንደዚሁ አይተወንም። ስለዚህም እግዚአብሔር የማይወደውን ኃጢአት የሆነውን ነገር ስናደርግ ቅጣት ይጠብቀናል ማለት ነው።

አዳምና ሄዋን ከኖሩ ብዙ መቶ ዓመታት ካለፉ በኋላ ሁልጊዜ ኃጢአትን የሚሰሩ ሰዎች በምድር ላይ ይኖሩ ነበር። እግዚአብሔር በእነዚህ ሰዎች ኃጢአት በጣም ያዝን ነበር፤ ስለፈጠራቸውም ይጸጸት ነበር። እግዚአብሔር የፈጠራትን ውብ ምድር አበለሻሿት፤ ጥሩ ባልሆነ ነገርም ሞሏት።

እግዚአብሔርም በዚህ ተቆጥቶ «ሰውን ከምድር ገጽ ላይ አጠፋለሁ። የሰዎች ክፋ ሥራ ሁሉ ያበቃለታል» አለ።







ኖኃና ቤተሰቦቹ ብቻ እግዚአብሔርን በመታዘዛቸው አስደሰቱት። አንድ ቀን እግዚአብሔር ምድርን የሚያጠፋ ውሃን እንደሚያመጣ ለኖኃ ነገረው። እግዚአብሔር ይህንን ጎርፍ የላከው የሰዎችን ኃጢአተኛነት ለመቅጣት ነበር።

እግዚአብሔርም ኖኃን፣ «ትልቅ መርከብ እንድትሰራ እፈልጋለሁ፤ ትክክለኛ መጠንና የመርከቡን አሰራር ሁሉ ደግሞ የምነግርህ እኔ ነኝ» አለው። ኖኃና ልጆቹ መርከቡን ጠንክረው ሰሩ። በእግዚአብሔር ያምኑ ነበርና በዘመኑ ለነበሩት ሰዎችና ስለሚመጣው የጥፋት ውሃ ቢናገሩም አንዳቸውም አልተቀበሏቸውም።


በመጨረሻም ልጆች! ከ120 ዓመታት በኋላ መርከቡ ተሰርቶ አበቃ። ኖኃና ቤተሰቡም እግዚአብሔር ሊያድናቸው ከሚፈልጋቸው እንስሳት ሁሉ ጋር በመሆን ወደ መርከቡ ገቡ። እግዚአብሔርም ጎርፍ ልኮ ምድርን ከዳር እስከዳር በውሃ ሸፈናት። ኃጢአተኞቹ ሰዎች ሁሉ ሰምጠው አለቁ። ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር በኃጢአተኛነታቸው ምክንያት ቀጣቸው። መርከቡ ውስጥ የነበሩት ብቻ ተረፉ።

እግዚአብሔርም በሰማይ ላይ ቀስተ ዳመናን በማሳየት ዳግመኛ ምድርን በውሃ እንደማያጠፋት ቃል ገባ። ልጆች! ቀስተ ዳመናን ባያችሁ ጊዜ ሁሉ ሁለት ነገሮችን አስታውሱ። ይኸውም ቅዱስ አምላካችን እግዚአብሔር ኃጢአተኛ የሆኑትን ሰዎች የቀጣቸው መሆኑንና ኖኃ እግዚአብሔርን በማመኑ ምክንያት ከነቤተሰቡ ከጥፋት ውሃው መዳኑን ነው። ለነ አዳም ተስፋ የተገባላቸው አዳኝ ይመጣል የተባለበት ከኖኃ የዘር ሀረግ በኩል መምጣት ነበረበት።

*«የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው» (ሮሜ 6፥23)*

## ልታስቡበት የሚገባ ነገር

ልጆች በህይወት ጉዞአችን የተሳሳተ አቅጣጫን ከያዝን ፍጻሜአችን ጥሩ አይሆንም። ችላ ብለነውም ይሁን ተሳስተን ከትክክለኛው መንገድ ከወጣን ስህተት ውስጥ እንገባለን። መጽሀፍ ቅዱስ የህይወታችንን የጉዞ አቅጣጫ እንድናስተካክል ስለአለፉት ዘመናት ሰዎች፣ ስለዛሬዎቹና ወደፊትም ስለሚኖሩት በማሳየት ያስተምረናል።




## የዕለቱ ጸሎት፦

እግዚአብሔር ዓለምን ከኃጢአት ጥፋት ለማዳን አዳኝ ለመላክ ተስፋ ቃል ስለሰጠን እመስግኑት።






# እግዚአብሔርን አዳኙን የመላክ የተስፋ ቃሉን ስለጠበቀ ተደንቃችሁ ታውቃላችሁ?

እግዚአብሔር በኖኃ ዘመን የነበሩትን ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት ያጠፋቸው ቢሆንም፣ የኖኃን ቤተሰብ ግን ለማዳን መርከብን አዘጋጅቶ ነበር። ልጆች! እግዚአብሔር ከዚህም ሌላ እኔንና እናንተን ለማዳንና ወደ እርሱ ለመመለስም ዐቅዶ ነበር። በዚህ ደግሞ በኖኃና ከእርሱ በተገኙት ትውልዶቹ አዳኙን ለመላክ አቅዶ ነበር። በመጨረሻም ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሔር አዳኙን ላከ። ያ አዳኝ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በጣም ህጻን ልጅ ሆኖ ሊወለድ ከሰማይ መጣ። እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደትወልድ የመረጠው ማርያም የተባለችውን ወጣት ድንግል ነበር። ማርያም ታዛዥና በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኘች ሴት ነበረች። እግዚአብሔር ተአምራዊ በሆነ መንገድ ማርያም ምንም ባል ሳታገባ ኢየሱስን እንድትጸንስ አደረገ። ኢየሱስ ክርስቶስን ለማሳደግም የሚረዳትን ዮሴፍ የሚባል ባልደረባ ሰጣት። ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያድግ ልክ እንደእናንተ ትምህርት ቤት መሄድ፣ ከጓደኞቹ ጋር መጫወትና ወላጆቹን ማገልገል ጀመረ።




ልጆች! ኢየሱስ ክርስቶስ ከእኔና ከእናንተ የተለየበት አንድ ነገር ግን ነበር። ይኸውም ምንም ኃጢአትን አለማድረጉ ነው። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ እኛ ስንወለድ ጀምሮ በልባችን የያዝነው ኃጢአት እርሱ ዘንድ አልነበረም። እግዚአብሔርን፣ ዮሴፍን፣ ማንንም አልታዘዘም ብሎ አያውቅም። ኢየሱስ ክርስቶስ በነገር ሁሉ ጻድቅ ነበር።

*«የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና......» (ሉቃ. 19፥10)*








## ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን ስለገለጠበት ሁኔታ ተደንቃችሁ ታውቃላችሁ?

የኢየሱስ መወለድ ተአምር ልክ አስቀድመው ነቢያት ተናግረውት እንደነበረው ነው የተፈጸመው። ኢየሱስ ከእግዚአብሔር መንፈስ የተወለደ በመሆኑ አወላለዱ እንደ እናንተ እና እኔ ዓይነት አልነበረም። ኢየሱስ ከእኛ የሚለይባቸው ሌሎች መንገዶችም አሉ። ኢየሱስ ንጹህ ነው፤ በስራውም ሆነ በንግግሩ ኃጢአትን አላደረገም። ተአምራትን በማድረግ፣ በሽተኞችን በመፈወስ፣ የዓይነ ስውራንን ዓይን በማብራትና ሽባዎችን በማዳን እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ለሰዎች አሳይቷል። ከዚህም ሌላ የሞቱ ሰዎችንም አስነስቷል። ኢየሱስ አንድ ትንሽ ልጅ የሰጠውን ምግብ ባርኮ 5000 ሕዝብን መግቦበታል። አውሎ ነፋስ የሚያናውጠውን ባህርም ጸጥ አድርጓል።

ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ስለሆነ የሚያስቸግረው አንድም ነገር አልነበረም። ለሰዎችም የእግዚአብሔርን ፍቅር አሳይቷል።



በኃጢአተኛነት ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን ይቅር ብሏቸዋል። እግዚአብሔር ለልጆች ያለውን ፍቅር ለማሳየት ኢየሱስ ህጻናትን ያቅፋቸው ነበር።



የሰዎች አስተሳሰብና ባህርይ ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት፣ እግዚአብሔር እንደሚፈልግ ኢየሱስ አስተምሯል። «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም አሳብህ ውደድ» ብሎ ተናግሯል። እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ኢየሱስን አዳኛቸው አድርገው በመቀበል ከኃጢአታቸው እንዲድኑ አስተምሯል። ኢየሱስ በስራውም ሆነ በንግግሩ ለእግዚአብሔር ፍጹም ታዛዥ ነበር። እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ወልድ ነው። ነገር ግን በኢየሱስ ያመነው ጥቂት ሰው ብቻ ነበር። አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስን ሰዎች ስለወደዱትና ስለተከተሉት በቁጣና በቅንአት ተሞሉ። ስለዚህም ኢየሱስን የሚያጠፉበትን ዘዴ ማሰብና ማቀድ ጀመሩ።




*«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፣ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና» (ዮሐ. 3፡16)*

## ልታስቡበት የሚገባ ነገር

ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ከኃጢአት ለማዳንና ይቅርታን ለማስገኘት፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው።

ልጆች! ከዚህ በታች የምታዩት ሥዕል ከላይ ወዳለው ስጦታ ሊለሚወስዳችሁ የምትደርሱበትን መንገድ ለማግኘት ሞክሩ።



## የዕለቱ ጸሎት፡-

ዓለምን ከኃጢአት ለማዳን ይኸንን ታላቅ ስጦታ ስለሰጠን እግዚአብሔርን እመስግኑ።





## ኢየሱስ አዳኝ ተብሎ በመጠራቱ ተደንቃችሁ ታውቃላችሁ?

ልጆች! ከሰዎች መካከል ያለ ማንኛውም ሰው አዳኛችን ሊሆን አይችልም። ለመሆኑ ኢየሱስ እናንተንና እኔን ከኃጢአታችን ለማዳን ምን ነበር ያደረገው? በአንድ ሌሊት ኢየሱስ ከጓደኞቹ ጋር እየተነጋገረ እያለ የሃይማኖት መሪዎች ዱላና ሰይፍ የያዙ ብዙ ሰዎችን ወደ እርሱ ላኩ። ሰዎቹም የመጡት ኢየሱስን ለማሰር ነበር።

«ጌታ ሆይ! እንዋጋቸው?» ሲሉ ጓደኞቹ ጠየቁት። «እኛምኮ ሰይፍ ይዘናል» ብሎ ከመካከላቸው አንደኛው የአንዱን ጆሮ ቆረጠው።

ነገር ግን ኢየሱስ «ተው!» ብሎ ከመጡት ሰዎች ጋር እንዳይጣሉ ከለከላቸው። ጆሮው የተቆረጠውን ሰውም ጆሮውን ልክ እንደ መጀመሪያው አድርጎ መለሰለት።

ወዲያውም ሰዎቹ ኢየሱስን እያዳፉ ጲላጦስ ወደተባለው ገዥ ወሰዱት። ከሃይማኖት መሪዎች መካከልም ኢየሱስን የሚጠሉት በሐሰት ከሰሱት። ወታደሮቹም ኢየሱስን ገረፉት፤ ራሱ ላይ የእሾኽ አክሊልን አድርገውም አሾፉበት።


ጲላጦስም እየሱስን አንዳንድ ጥያቄዎችን ከጠየቀው በኋላ ለህዝቡ ኢየሱስ ላይ ምንም ጥፋት እንዳላገኘ ነገራቸው። ህዝቡ ግን «እስወግደው! ስቀለው!» እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም በመስቀል ላይ እንዲሰቅሉትና እንዲገድሉት አሳልፎ ሰጣቸው።

ልጆች! ኢየሱስ ምንም ጥፋት አልሰራም ነበር። እርሱ እግዚአብሔር ወልድ ነበር። ኃጢአት የሌለበት ፍጹምና ንጹህ የሆነ ሰውም ነበር። ነገር ግን እንዲህ ሆኖ እንዲሞት የእግዚአብሔር የራሱ እቅድ ነበር። እርሱም ይህንን ያደረገው አዳኝ ለመላክ የሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም ነበር።

*«...ራሱን አዋረደ፤ ለሞትም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ» (ፊልጵ. 2፥8)*







## ኢየሱስ እንዴት ሆኖ እንደሞተ አስባችሁና ተደንቃችሁ ታውቃላችሁ?

ልጆች! ምናልባት ኢየሱስ እንዴት ሆኖ እንደሞተ አታውቁ ይሆናል፤ ወይም ደግሞ ይህ ዓይነቱ ጻድቅ ሰው ለምን ይሞታል? ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል። ኢየሱስ መስቀል ቀራንዮ ወደ ተባለ ቦታ ተወሰደ። ወታደሮችም እጁንና እግሩን በመስቀል ላይ በምስማር ቸነከሩት፤ ሰቀሉትም። ሰዎች ሁሉ ተሰብስበው ተዘባበቱበት፤ ይቀልዱበትና የሚያበሳጭ የስድብ ንግግርን ይናገሩት ነበር። እንዴት ያለ ከባድ ስቃይ ነው። የኢየሱስም ሰውነት ደማ።

በዚያች ቀን ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተበት ጊዜ እግዚአብሔር የዓለምን ኃጢአት ሁሉ በእርሱ ላይ አደረገበት። በሰዎች ውስጥ ያለ የጥላቻ፣ የመዋሸት፣ የመገዳደልና የሌሎችም ኃጢአቶች ሁሉ በጌታ ኢየሱስ ላይ ተጫነበት። እርሱ መሞት አይገባውም ነበር፤ ነገር ግን የእኔንና የእናንተን ፍርድ በመውሰድ በመስቀል ላይ ሞተልን።

መጽሐፍ ቅዱስ *«ደም ሳይፈስ ስርየት የለም»* ይላል (ዕብ. 9፥22) ኢየሱስ ውድ የሆነ ደሙን አፍስሶ የእኛን ቅጣት ባይወስድልን ኖሮ የኃጢአታችንን ይቅርታ አናገኝም ነበር።

ኢየሱስ መስቀል ላይ ሆኖ ሲሞት፣ ልክ በስድስት ሰዓት ላይ በአገሪቱ ሁሉ ጨለማ ሆነ። ኢየሱስም «አምላኬ! አምላኬ! ለምን ተውከኝ?» ብሎ ጮኸ። ቅዱስና ንጹህ እግዚአብሔር ግን ወደ ልጁ ወደ ኢየሱስ መመልከት አልቻለም። ምክንያቱም የዓለም ሁሉ ኃጢአት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሆኖ ነበርና።

ከዚህም በኋላ ኢየሱስ «አባት ሆይ! ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ» ብሎ ሞተ።

የሆነውን ነገር ሁሉ አስተውሎ የተመለከተ አንድ ወታደርም «ይህ በእርግጥም የእግዚአብሔር ልጅ ነው!» ብሎ ጮኸ።

ልጆች! ኢየሱስ በመስቀል ላይ የኃጢአትን ቅጣት ሁሉ በወሰደ ጊዜ፣ አዳኝ እንደመባሉ መጠን ሊያደርግ የሚገባውን ነገር ሁሉ አድርጓል።

*«..... ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአተኛ አደረገው» (2 ቆሮ 5፥21)*





## ልታስቡበት የሚገባ ነገር

ልጆች! ጓደኞቻችሁን ስለምትወዱትና ስቃዩን ማየት ስለማትፈልጉ «ስለአንተ ቅጣት እኔ እቀጣለሁ» ብላችሁ ታውቃላችሁ? ኢየሱስ ታዲያ ልክ እንደዚህ ነው ያደረገላችሁ።

ልጆች! ነጠብጣብ ያለበትን እያንዳንዱን ቦታ ቀለም ቀቡት።



## የዕለቱ ጸሎት፦

እግዚአብሔር ሁልጊዜ ጸሎታችሁን ይሰማል፤ ይጠነቀቅላችኋል። ስለዚህ በየቀኑ ከእርሱ ጋር በጸሎት እንድትነጋገሩ እንዲያስታውሳችሁ ጠይቁት።

## ኢየሱስ ከሞቱ በኋላ ህያው ስለመሆኑ ተደንቃችሁ ታውቃላችሁ?

የኢየሱስ ተከታዮች ሬሳውን ወስደው ቀበሩት። የኢየሱስን ሬሳ ማንም እንዳይሰርቀው ለማድረግ ወታደሮች እንዲጠብቁ ታዝዘው ነበር። በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን በማለዳ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ተፈጠረ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድም አንድ መልአክ ተልኮ የመቃብሩን መዝጊያ ድንጋይ አንከባለለው። በዚህ ጊዜ መቃብሩን ይጠብቁ የነበሩት ወታደሮች ከመደንገጣቸውና ከመፍራታቸው የተነሳ ተንቀጠቀጡ! መንቀሳቀስም ሆነ መናገር አልቻሉም ነበር።






የኢየሱስ ወዳጆች የነበሩ ጥቂት ሴቶች ሬሳውን ሽቶ ለመቀባት ወደ መቃብሩ መጡ። የመቃብሩን ድንጋይ ተንከባልሎ ባዩት ጊዜም መቃብሩ ውስጥ ጌታ መኖሩን ለማወቅ ተጣደፉ። በዚህ ጊዜም መልአኩን አዩት።

መልአኩም «አትፍሩ፣ የተሰቀለውን ኢየሱስን ፈልጋችሁ እንደመጣችሁ አውቃለሁ። እርሱ እዚህ የለም፤ እንደተናገረው ከሞት ተነስቷል። ፈጥናችሁ ወደ ደቀመዛሙርቱ ሂዱና መነሳቱን ንገሯቸው።» አላቸው። ሴቶችም ይህንኑ ለኢየሱስ ወዳጆች ለደቀ መዛሙርቱ ለመንገር እየሮጡ ሄዱ።

ከዚህ በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ስለኢየሱስ እየተነጋገሩ እያለ ኢየሱስ ራሱ ድንገት ወደክፍላቸው ገብቶ በመካከላቸው ቆመ። «ሰላም ለእናንተ ይሁን!» አላቸው። ደቀ መዛሙርቱ ፈሩ። ኢየሱስ ግን





«እጆቼን ተመልከቱ፣ እግሮቼንም እዩ። እኔ ኢየሱስ መሆኔን ማረጋገጥ ትችላላችሁ። ዳስሳችሁኝ መንፈስ አለመሆኔን ማወቅ ትችላላችሁ» አላቸው።

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለብዙ ሳምንታት አብሯቸው ኖረ። ከ500 ለሚበልጡ ሰዎችም ታይቶ ከሞት የተነሳ መሆኑን ሰዎች እንዲያውቁት አደረገ። አንድ ቀንም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሚያስተምራቸውንና የሚነግራቸውን ተናግሮ ሲያበቃ፣ ወደ ሰማይ ሲያርግና ደመና ሲጋርደው ደቀ መዛሙርቱ ተመለከቱ። ልጆች! ኢየሱስ ከሞት ተነስቶ ቀድሞ ወደ ነበረበት ወደ መንግስተ ሰማይ በመሄድ አሁን በዚያ ይኖራል።

እግዚአብሔር ካለው ታላቅ ኃይል የተነሳ፣ ኢየሱስን ከሞት አስነስቶታል። እርሱንም አዳኝ አድርጎ በመላክ ዓለምን ከኃጢአት ለማዳን የገባውንም ቃል ኪዳን ጠብቋል።

*«..... መጽሀፍ ቅዱስ እንደሚለው ክርስቶስ ስለኃጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረም፤ መጽሀፍም እንደሚል በሶስተኛው ቀን ተነሳ....» (1ቆሮ. 15፥3-4)*



## ልታስቡበት የሚገባ ነገር

ልጆች! አስቀድሙን በተማርነው መሰረት ኢየሱስ መሞት የነበረበት ለምን ነበር?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________


ኢየሱስ ለሶስት ቀናት ሞቶ ከቆየ በኋላስ ምን ሆነ?

________________________________________

________________________________________


________________________________________

________________________________________



### የእለቱ ጸሎት፦

ልጆች! አስደናቂ ስለሆነው የእግዚአብሔር ስጦታ ብዙ ማወቅ እንድትችሉ እንዲረዳችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት።



## ልጆች! ኢየሱስ እንዴት የግል አዳኛችሁ እንደሆነ ተደንቃችሁ ታውቃላችሁ?


አሁን ኢየሱስ ስለኃጢአታችሁ እንደሞተ አውቃችኋል። ምናልባት አሁን ኃጢአታችሁ ይቅር እንዲባል ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ማወቅ ትፈልጉ ይሆናል። ኢየሱስም ለዓለም ሁሉ ኃጢአት መሞቱንና ከሞት መነሳቱን ማወቅ ራሱ አስደናቂ ነገር ነው። ነገር ግን ልጆች! ኢየሱስ ስለእናንተ መሞቱ ን ታውቃላችሁ? ኢየሱስ የእያንዳንዳችሁ የግል መድሃኒት መሆን ይፈልጋል። ራሳችሁን በራሳችሁ ከኃጢአት ማዳን አትችሉም። ጥሩ ጥሩ ስራዎችን በመስራት ከኃጢአት ቅጣት ማምለጥ አትችሉም። ጸሎትን በማነብነብ፣ ለድኾች ምጽዋት በመስጠት፣ መጥፎ ነገር ባለመናገር፣ ጥሩ ያልሆነ ስራን ባለመስራት ሁሉ የኃጢአትን ይቅርታ ማግኘት





አትችሉም። የእግዚአብሔር ይቅርታ ማግኛው መንገድ አንድ ብቻ መሆኑንና እርሱም ልጁ ኢየሱስ እንደሆነ ይናገራል።

መጽሀፍ ቅዱስ በሀዋርያት ስራ 16፥31 ላይ «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰቦችህም ትድናላችሁ» ይላል። ልጆች! ማመን ማለት ሙሉ ለሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ መታመንና የእርሱ ተከታይ መሆን ማለት ነው። እግዚአብሔር የተቀበለው የኃጢአታችሁ ቅጣት የኢየሱስ ክርስቶስን የመስቀል ሞት ብቻ ነው። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ለመታመንና የግል መድኃኒታችሁ መሆኑን ለማመን ስትወስኑ እግዚአብሔር «ድናችኋል» ይላችኋል። በኃጢአታችሁ ከመጠየቅና ከመቀጣትም ነጻ ትወጣላችሁ። ስትሞቱም ከእግዚአብሔር በመለየት ወደ መቀጫው ቦታ አትወሰዱም። በምትኩ ግን፣ አንድ ቀን ከእግዚአብሔር ጋር በሰማይ ለዘላለም መኖር ትጀምራላችሁ።



ልጆች! በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመንና የእርሱ ተከታይ ለመሆን ትፈልጋላችሁ? የምትፈልጉ ከሆነ ለእግዚአብሔር አሁኑኑ ልትነግሩት ትችላላችሁ። ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የሚመሳሰል ጸሎት መጸለይ ትችላላችሁ።

«ውድ እግዚአብሔር፤ ኃጢአተኛ መሆኔን አውቃለሁ። ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኃጢአቴ ለመቀጣት እንደሞተ አምኛለሁ። ከሞት እንዳስነሳኸውም አምናለሁ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የግል መድኃኔቴ እንዲሆንና ኃጢአቴ ይቅር እንድባል እፈልጋለሁ። ስለወደድከኝና ከሚገባኝ ቅጣት ስላዳንከኝ አመሰግንሃለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፤ አሜን።»

ልጆች! በእውነተኛነት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የግል አዳኛችሁ እንደሆነ ካመናችሁ የዳናችሁ መሆኑን እግዚ አብሔር አረጋግጦላችኋል። ኃጢአታችሁ ይቅር ተብሏል። ኢየሱስም በመንፈስ በህይወታችሁ ውስጥ ሊኖር ወደ እናንተ መጥቶአል።

«እኔ (ኢየሱስ) መንገድና እውነት ህይወትም ነኝ፤ በእኔ በኩል በቀር ወደ አብ (እግዚአብሔር) የሚመጣ የለም» (ዮሐ. 14፥6)




## ኃጢአታችሁን ይቅር ለመባል
## የእግዚአብሄርን መንገድ ተከትላችኋል?

ይቅር
መባል

3. ኃጢአትን ይቅር ማለት የሚችለው
ጌታ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን አምንሃል?
አምኛለሁ____ አላመንኩም______



4. እነኚህን ደረጃዎች ሁሉ ካለፍህ
አንድ ቀን በመንግስተ ሰማይ
ከእግዚአብሔር ጋር መሆን ትችላለህ!



ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል መድኃኒትህ
አድርገህ ከተቀበልህ፣ በየደረጃው ያሉትን
የእግር (የጫማ) ምልክቶች ቀለም ቀባቸው ።

2. እግዚአብሔር እንደሚወድህ፣ የኃጢአትህን
ዋጋ ለመክፈል ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል
ላይ እንደሞተልህ እና ከሞትም እንደተነሳ
ታምናለህ?

አምናለሁ________ አላምንም________

መ
ነ
ሻ

1. ኃጢአተኛ መሆንህን
እምነህ ተቀብለሀል?
ተቀብያለሁ____ አልተቀበልኩም____

ኃጢዓት

መንግስተ ሰማይ

# ኢየሱስ ከኃጢአት እንዳዳናችሁ ማወቅ ትችላላችሁ

ልጆች! ከኃጢአታችሁ ቅጣት ድናችኋል? «አዎን» ካላችሁ እንዴት አወቃችሁ? የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰብዎችህም ትድናላችሁ» ይላል (የሐዋ. 16፥31)። ልጆች! እዚህ ጥቅስ ውስጥ የራሳችሁን ስም ማስገባት ትችላላችሁ። «__________________ *(ስም)* በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ __________________ *(ስም)* ይድናል» ማለት ትችላላችሁ። ልጆች! ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዳለ በእውነተኛነት ብታምኑ (በእርሱ ላይ በፍጹም ብታምኑ) ከኃጢአት ቅጣት የዳናችሁ መሆኑን፣ እግዚአብሔር በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ቃል ገብቶላችኋል።

በኢየሱስ ያመናችሁ ከሆነና የእርሱ ተከታዮች ከሆናችሁ፣ ይህንን ውሳኔ የወሰናችሁበትን የዛሬውን ቀን ጻፉት፤ ይህም ሁሌ እንድታስታውሱት ይረዳችኋል።

በዚህ እለት ኢየሱስ የግል መድኃኒቴ እንደሆነ እምኛለሁ።

ቀን __________________





ልጆች! አሁን ጌታ ኢየሱስ የግል መድታኒታችሁ ሆኗል፤ እርሱ ለእናንተ። ሌላ ተስፋም አለላችሁ፤ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር «.. አልለቅህም ከቶም አልተውህም...» ዕብ. 13፥5 ይላል። አሁንም ልጆች ስማችሁን በዚህ ጥቅስ ውስጥ ማስገባት ትችላላችሁ። «(ስም) አልለቅህም ከቶም አልተውህም።» በህይወታችሁ ውስጥ ለመኖር በመንፈሱ ወደ እናንተ የመጣው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይተዋችሁም። ሁልጊዜ እግዚአብሔርን እያስደሰታችሁትና ትክክለኛ የሆነውን ነገር እያደረጋችሁ ስትኖሩ ሊረዳችሁ ከእናንተ ጋር ይሆናል። ከላይ ባየነው የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ቀጥሎ ያለው ጥቅስ ሌላ ተጨማሪ ቃል ኪዳን ይዟል። «ጌታ ይረዳሃልና....» ዕብ. 13፥6። ልጆች! እግዚአብሔር የሚረዳችሁ ምን እንድታደርጉ ነው? እግዚአብሔር የሚረዳችሁ እንድት ታዘዙና የእግዚአብሔር ጠላት የሆነውን ሰይጣንን «አልታዘዝህም» እንድትሉት ነው። ኢየሱስ ከኃጢአት ቅጣት ያዳናችሁ መሆኑን ማወቅ እንዴት ያለ አስደናቂ ነገር ነው።

*«የዘላለም ሀይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።» (1 ዮሐ. 5፥13)*



## ጠላት እንዳላችሁ ታውቃላችሁ?

ልጆች! ሰይጣን ትልቁ ጠላታችን ነው። መጽሀፍ ቅዱስ ሰይጣን በእግዚአብሔር የተፈጠረ ውብ መልአክ እንደ ነበር ይናገራል። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር በመጣላት የእግዚአብሔርን እቅድ ለማፍረስ ይፈልግ ጀመር። ሄዋንን በማታለል ወደ ዓለማችን ኃጢአት እንዲገባ ያደረገውም እርሱ ነው። የእግዚአብሔርን ውብ ፍጥረት በኃጢአት አበላሸው። ልጆች! ሰይጣን ዲያቢሎስ ተብሎ ይጠራል። ከመጀመሪያው ጀምሮ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን እንዳ ይፈጽምና አዳኙን ልኮ ዓ ለምን ከኃጢአት እንዳያድን ለማድረግ ብዙ ጥሯል። ነገር ግን ሰይጣን አልተሳካለትም። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞቱና ከሞትም በመነሳቱ ሰይጣንን አሸነፈው።

ሰይጣን እግዚአብሔርን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኛቸው ያደረጉትን ሰዎች ሁሉ አይወድም።






ልጆች! ሰይጣን ትክክል ያልሆኑ ነገሮችን እንድንሰራ ለማድረግ ይሞክራል። ተጠራጣሪዎች እንድንሆንና ጥሩ ያልሆኑ ነገሮችን እንድናስብ ያደርጋል። ጌታ ኢየሱስን እንድንወድም አይፈልግም። ነገር ግን ልጆች ኢየሱስ አዳኛችሁ እንደሆነ ካመናችሁ ሰይጣንን መፍራት የለባችሁም። መጽሀፍ ቅዱስ በ1 ዮሐ. 4፥4 ላይ «በዓለም ካለው (ከሰይጣን) ይልቅ በእናንተ ያለው (መንፈስ ቅዱስ) ይበልጣል» ይላል። ልጆች ኢየሱስ ራሱ እግዚአብሔር ነው፤ ከሰይጣን የበለጠ ኃይለኛ ነው። አንድ ቀን ሰይጣንና እርሱን የሚከተሉ ሁሉ ለዘላለም ይቀጣሉ። ኢየሱስ በህይወታችሁ ውስጥ እስካለ ድረስ፣ ጠላታችሁን ሰይጣንን እንዴት እንደምታሸንፉ ያስተምራችኋል።

*«በመጠን ኑሩ፣ ንቁም፣ ባላንጋራችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን ለማግኘት እንደተራበ አንበሳ ይንጎራደዳልና፤» (1ኛ ጴጥ. 5፥8)*

## ልታስቡበት የሚገባ ነገር

ልጆች! ታጢአታችሁ ይቅር መባሉን እንዴት ልታውቁ ትችላላችሁ? ትክክል ያልሆነን ነገር ስትፈጽሙ ማድረግ ያለባችሁ፦




### የዕለቱ ጸሎት፦

ልጆች! እግዚአብሔር ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲልና እንዲያድናችሁ ከጠየቃችሁት ለዘላለም ልጆቹ ስለሚያደርጋችሁ አመስግኑት። የሰማዩ አባታችሁ ይወዳችኋል። ትክክል ያልሆነን ነገር ባደረጋችሁ ጊዜ ሁሉ መሳሳታችሁን ለእርሱ ንገሩት።





## በጠላታችሁ ላይ እንዴት ድልን እንደምትቀዳጁ ማወቅ ትችላላችሁ!

ልጆች! በእርግጥ በየቀኑ ሰይጣንን ታሸንፉታላችሁ? ያላሸነፋችሁት ከሆን ምንድነው የሚሆነው? ሰይጣን ኃጢአትን እንድትሰሩና ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁ ኅብረት እንዲበላሽ ይፈልጋል። ሰይጣንን ድል ለማድረግ የሚረዳችሁን አራት አስፈላጊ ነገሮች ማስታወስ ይኖርባችኋል።

(1) ኃጢአትን መስራት የለባችሁም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞትና ሞትን ድል አድርጎ ሲነሳ ሰይጣንንና ኃጢአትን እንዳ ሸነፈ አስተውሉ። መጽሀፍ ቅዱስ በያዕቆብ 4፤7 ላይ «ዲያቢሎስን ተቃወሙት፣ ከእናንተም ይሸሻል» ይላል። በህይወታችሁ ውስጥ ባለው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል አማካይነት «ኃጢአትን አልሰራም» ማለት ትችላላችሁ።

(2) ኃጢአት እግዚአብሔር ጋር ያላችሁን ግንኙነት እንደሚያበላሸው አስታውሱ። ልጆች! እግዚአብሔር መቼውንም ቢሆን አይተዋችሁም፣ ነገር ግን ኃጢአትን ብታደርጉ ያዝናል። እንደዚሁም ደግሞ ኃጢአት ጸሎታችሁ ወደ እግዚአብሔር እንዳይደርስና መልስ እንዳታገኙ ይከለክላል።

(3) ኃጢአት የሰራችሁ እንደሆነ ኃጢአታችሁን በእግዚአብሔር ፊት በመናዘዝ የተበላሹትን ነገሮች ማስተካከል ትችላላችሁ። መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት እንደሰራችሁ ስትናገሩ እግዚአብሔር ደግሞ ይቅር እንደሚላችሁ የተጻፈ ቃል ኪዳን አለ። ከዚህ በኋላም ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁን ግንኙነት ማስተካከል ትችላላችሁ። ዳግመኛ ተመሳሳይ ኃጢአትን እንዳትሰሩ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጠይቁት። ከዚህም በተጨማሪ ኃጢአትን በመሥራታችሁ የጎዳችሁትን ሰው ይቅርታ መጠየቅ አለባችሁ።

(4) ሰይጣንን ድል ማድረግ እንድትችሉ ስለረዳችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑት። ኢየሱስ ባለድል ሊያደርጋችሁ የሚችል ብቸኛው መንገድ መሆኑን አትዘንጉ።

መጽሀፍ ቅዱስ በኤፌሶን 6፥10 ላይ «... በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ» ይላል። ልጆች በሰይጣን ላይ ስላላችሁ ድል የማድረግ ኃይል በደምብ ማወቁ በጣም ጥሩ ነው፤ አይደል?

*«ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሳትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።» (1 ቆሮ. 15፥57)*








## እግዚአብሔር ጸሎታችሁን እንደሚሰማና መልስን እንደሚሰጥ ማወቅ ትችላላችሁ።

ለመሆኑ ጸሎት ምንድነው? ስለምንስ ነው መጸለይ የምትችሉት? ጸሎት የራሳችሁን አሳብ በራሳችሁ ቋንቋ ለእግዚአብሔር መናገር ነው። ጸሎት የሚሸመደድና የሚጠና የተለመደ ንግግር አይደለም። እግዚአብሔር በየእለቱ እንድታነጋግሩት ይፈልጋል። «ዛሬ ስራ ስለበዛብኝ መስማት አልችልም» አይልም።

ልጆች! በፈለጋችሁበት ጊዜ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ትችላላችሁ። መጽሀፍ ቅዱስ «ሳታቋርጡ ጸልዩ» ይላል (ተሰሎ 5፥17) እየሮጣችሁም፣ እየተጫወታችሁም መጸለይ ትችላላችሁ። ለምሳሌ ምግብ ከመብላታችሁ በፊት «እግዚአብሔር ሆይ! ይህንን ጥሩ ምግብ ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ» ማለት ትችላላችሁ። የታመመ ሰው ካጋጠማችሁ «ውዱ እግዚአብሔር ሆይ! እባክህን ወዳጄን ፈውሰው» ብላችሁ መጸለይ ትችላላችሁ።



ፍርሃት ሲሰማችሁ እግዚአብሔር ፍርሃታችሁን እንዲያስወግድ ጠይቁት። ከዚህ ሌላም ስለእግዚአብሔር የበለጠ ማወቅ እንድትችሉ እግዚአብሔር ራሱ እንዲረዳችሁ መጸለይ ትችላላችሁ።

ልጆች! እግዚአብሔር የሚሰማችሁን ነገር እንድትነግሩት ይፈልጋል። ደስ ሲላችሁም ስታዝኑም፣ ጥሩ ያልሆነ ነገር ስርታችሁ ስትጸጸቱም ለእግዚአብሔር ንገሩት። እርሱ ሁልጊዜም ኃጢአታችሁን ይቅር ይላችኋል። ትክክል የሆነውን ነገር ብቻ እንድታደርጉ ኃይል በመስጠት እንዲረዳችሁም እግዚአብሔርን ጠይቁት።

እግዚአብሔር ሁሌም ስትጸልዩ ይሰማችኋል። ነገር ግን ልጆች! ሁልጊዜ የጠየቃችሁትን ነገር ሁሉ አይሰጣችሁም። አንዳንድ ጊዜ ስጠይቁት «አልሰጥህም፣ ምክንያቱም ይሄ ለእናንተ ጥሩ አይደለ ም» ይላል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ልክ እንደጠየቃችሁት ወዲያውኑ «እሺ!» ብሎ ይሰጣችኋል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር «ቆዩ፣ ታገሱ፣ ጊዜው አይደለም» ብሎ ይመልስላችኋል። ልጆች! ማወቅ ያለባችሁ ነገር ግን እግዚአብሔር ለእናንተ የሚጠቅመውን ነገር የሚያደርግ መሆኑን ነው። አስታውሱ ልጆች! እግዚአብሔር ሁልጊዜ ጸሎታችን ሰምቶ መልስ ይሰጣችኋል።

*«በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ» (ፊልጵ. 4፡6)*




## ልታስቡበት የሚገባ ነገር

ልጆች ኃጢአትን ድል ማድረግ ትችላላችሁ። እግዚአብሔር በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ባለድል እንደምንሆን ቃል ኪዳን ገብቶልናል።

**የእስቱ ጸሎት፦**

እግዚአብሔር በኃጢአት ውጊያ ላይ ለማሸነፍ እንድትችሉ፣ ጉልበትና ኃይልን ስለሰጣችሁ አመስግኑት።




# እግዚአብሔርን የበለጠ ማወቅ ትችላላችሁ

ልጆች! ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችሁ እንደሆነ ካመናችሁ ጊዜ ጀምሮ፣ እግዚአብሔር የበለጠ እንድታውቁት ይፈልጋል። እግዚአብሔርን ለማወቅ የምትችሉበት አንደኛው መንገድ በየቀኑ ለተወሰነ ሰዓት መጽሀፍ ቅዱስን ማንበብና ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት በመነጋገር ነው። ይህም «የጥሞና ጊዜ» ተብሎ ይጠራል።

የጥሞና ጊዜያችሁን በየቀኑ፣ በተወሰነ ሰዓት ለማድረግ ማቀድ ትችላላችሁ። ይህ መደበኛ የጥሞና ጊዜ ጠዋት እንደተነሳችሁ ወይም ደግሞ ልትተኙ ስትሉ ሊሆን ይችላል። ለጥሞና ጊዜያችሁ የተመቸና ሌሎች ሰዎች ሊረብሿችሁ የማይችሉበትን ቦታ ምረጡ።

የጥሞና ጊዜያችሁን ስትጀምሩ እግዚአብሔር የሚያስተምራችሁን መረዳትና መታዘዝ እንድትችሉ እንዲረዳችሁ በጸሎት ጠይቁት። እንደዚሁም ኃጢአታችሁን በመናዘዝ ከእግዚአብሔር ለመማርና ለመታዘዝ ራሳችሁን አዘጋጁ።







ልጆች! ምናልባት መጽሀፍ ቅዱስ የሌላችሁ ከሆነ እዚህ መጽሀፍ ውስጥ ካሉት የሚነበቡ ጥቅሶች መካከል ጥቂቶችን ለይታችሁ በማውጣት በዝግታና በማስተዋል አንብቧቸው። አንዳንዶቹ ጥቅሶች ልታምኑባቸው የሚገቡ ቃል ኪዳኖች ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ ልትታዘዟቸው የሚገቡ መመሪያዎች ናቸው። በምታነቧቸው ጊዜ ትርጉማቸው ምን እንደሆነና እግዚአብሔር እንድትታዘዙት የሚፈልገው ምንን በተመለከተ እንደሆነ ራሳችሁን ጠይቁ። በሳምንት አንድ ጥቅስ በቃላችሁ ለመያዝና የተጻፈውን ሳታነቡ በቃላችሁ ለማለት ጥቂት የጥናት ጊዜ መድቡ።

የጥሞና ጊዜያችሁ ማጠቃለያ ጸሎት ነው። ያነበባችሁትን ጥቅስ በተመለከተ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገሩ። ቃሉን መታዘዝ እንድትችሉ እንዲያስታውሳችሁና እንዲረዳችሁም ጠይቁት። ይህ የጸሎት ጊዜያችሁ በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ስለጸሎት የተማራችሁትን ነገር የምትፈጽሙበትም ሊሆን ይችላል። ልጆች! በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር የምትገናኙበት የጥሞና ጊዜ ካላችሁ እግዚአብሔርን ሁሌም የበለጠ እያወቃችሁት ትሄዳላችሁ። እግዚአብሔርን የበለጠ ባወቃችሁ መጠንም እርሱ የሚወደውንና የሚፈልገውን አይነት ሰው እየሆናችሁ ትሄዳላችሁ።

*«በማታና በጥዋት በቀትርም እናገራለሁ፤ እጮኻማለሁ፤ ቃሌንም ይሰማኛል» (መዝ. 55፥17)*

# ልክ እንደ እናንተ ኢየሱስን የሚወዱ ሌሎች ሰዎችም አሉ


ልጆች! አንዳንድ ጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ የምታምኑ እናንተ ብቻ እንደሆናችሁ ታስባላችሁ አይደል? ምድር ስትፈጠር ጀምሮ እግዚአብሔርን የሚወዱና ቃሉን የሚታዘዙ ሰዎች አሉ። ልክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችሁ እንደሆነ ስታምኑ በዓለም ዙሪያ ካሉት ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንደዚሁም ታላላቅ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ከሆኑት ሰዎች መካከል ትቀላቀላላችሁ። የእግዚአብሔር የሆኑ ሰዎች ደግሞ እርስ በርሳቸው ይፋቀራሉ።

ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆኑ ሰዎች ኅብረት ያደርጋሉ። አብረው ይጸልያሉ፤ መዝሙር ይዘምራሉ፤ ስለ እግዚአብሔር የበለጠ ለማወቅና እርስ በእርሳቸው እንዴት መረዳዳት እንዳለባቸውም የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን መጽሀፍ ቅዱስ ያጠናሉ። እነኚህ ሰዎች የት የሚሰባሰቡ ይመስላችኋል? ቤት ውስጥ ወይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሰባሰብ ይችላሉ።

ልጆች! ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችሁ እንደሆነ የምታምኑት እናንተ ብቻ እንዳልሆናችሁ አስታውሱ። በምትኖሩበት አካባቢ ሌሎችም ኢየሱስ ክርስቶስን የሚወዱ ሰዎች ይኖራሉ። ወደ እነዚህ በክርስቶስ ወንድሞቻችሁና እህቶቻችሁ ወደ ሆኑ ሰዎች እንዲመራችሁና እንዲያገኛችሁ እግዚአብሔርን ልትጠይቁት ትችላላችሁ።

*«..... እንደወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ....» (ዮሐ. 13፥34)*





ልጆች ቀጥሎ የተጻፉት አርፍተ ነገሮች **እውነት** ወይም **ሀሰት** መሆናቸውን አረጋግጣችሁ በባዶ ቦታው ላይ መልሱ።

1. የ «የጥሞና ጊዜ» ከመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅስ የሚነበብበትና ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት የሚነጋገሩበት ጊዜ ነው_______
2. የትም ቦታ ሆናችሁ መጸለይ ትችላላችሁ_______
3. እግዚአብሔር የሚሰማችሁ ጠዋት ስትጸልዩ ብቻ ነው_______
4. እግዚአብሔር በጸሎት ለምንጠይቀው ጥያቄ ሁሉ «እሽ» የሚል መልስ ይሰጠናል_______
5. እግዚአብሔር ለሚገጥማችሁ ችግር ሁሉ ይጠነቀቅላችኋል_______
6. በጥሞና ጊዜያችሁ እግዚአብሔርን ዘወትር በተሻለ ሁኔታ እያወቃችሁት ትሄዳላችሁ_______
7. የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ አስፈላጊ አይደለም_________



መልስ
1. እውነት 2. እውነት 3. ሐሰት 4. ሐሰት
5. እውነት 6. እውነት 7. ሐሰት




ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥቅሶች ከገጽ 63-64 ጋር በማነጻጸር እግዚአብሄርን እንዴት መታዘዝ እንደምትችሉ ቀጥሎ ባለው ባዶ ቦታ ላይ ሙሉ። ለምሳሌ እንዲሆናችሁ ተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው ተሰርቶላችኋል።

1. **ኤፌሶን** 4፥32
2. 2 **ጢሞቴዎስ** 2፥15
3. **ማቴዎስ** 5፥44
4. **ኤፌሶን** 4፥28
5. 1 **ተሰሎንቄ** 5፥18
6. **ፊልጵ**. 4፥4

## እግዚአብሔር ቀጥሎ ያሉትን ነገሮች በማድረግ እንድንታዘዘው ይፈልጋል።

1. ቸርና ይቅር ባይ መሆን (ኤፌሶን 4፥32)
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________
5. ______________________________
6. ______________________________

**ልጆች! እግዚአብሔር ቃሉን እንድትታዘዙ እንዲረዳችሁ ጠይቁት።**




# የእግዚአብሔር ምስክሮች እንደሆናችሁ ታውቃላችሁ?

ልጆች! ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችሁ ሆኖ እንደለወጣችሁ ታውቃላችሁ? መጽሀፍ ቅዱስ በ2 ቆሮ 5፥17 ላይ «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል» ይላል። እግዚአብሔርን እያወቃችሁት በሄዳችሁ መጠን በህይወታችሁ ብዙ ነገሮች መለወጥ ይጀምራሉ። እግዚአብሔር ደስ የማይሰኝባቸውን እንደመዋሸትና ከሌሎች ጋር መጣላት የመሳሰሉ ነገሮችን ላለማድረግ መጣር አለባችሁ። በምትኩ እግዚአብሔርን የሚያስደስቱ እንደ ሩህሩህ መሆንና ጓደኞቻችሁን መርዳት የመሳሰሉ ነገሮችን ማድረግ አለባችሁ።

ሌሎች ሰዎች ህይወታችሁን ሲመለከቱም መለወጣችሁን ያስተውላሉ። እነኚህ ሰዎች የህይወታችሁን መለወጥ፣ ፍቅር፣ ርህራሄና ታማኝነት የሞላባችሁ መሆናችሁን ወይም ደግሞ አስቀድማችሁ ታደርጓቸው የነበሩትን መጥፎ ስራዎች መተዋችሁን ሲያዩ፣ እንደዚህ የተለወጣችሁበትን ምክንያት ማወቅ ይፈልጋሉ።

ታዲያ በዚህ ጊዜ ልጆች! እግዚአብሔር በህይወታችሁ ውስጥ እንዴት ለውጥ እንዳመጠ ልትነግሯቸው ትችላላችሁ። ከእነኚህ ሰዎች መካከልም አንዳንዶቹ ልክ እንደ እናንተ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው ማመን ይፈልጉ ይሆናል። ስለዚህም ድርጊታችሁና ንግግራችሁ በአንድነት ሌሎች ሰዎች ስለ ክርስቶስ እንዲያውቁ ምስክር መሆን ይችላል ማለት ነው።

*«መልካሙን ስራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ»*
*(ማቴ. 5፥16)*






## ስለእግዚአብሔር መከራን ስትቀበሉ፣ እርሱ እንዴት እንደሚያበረታችሁ ታውቃላችሁ

ልጆች! አንዳንድ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው የማያምኑ ሰዎች ስለ እርሱ መከራን መቀበላቸው ግዴታ ይሆናል። ከጥንት ጀምሮ ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ስለ ክርስቶስ መከራን ተቀብለዋል።

ኢየሱስ ወደ መንግስተ ሰማይ ከተመለሰና ካረገ በኋላ፣ እስጢፋኖስ የተባለ ወጣት ሰው ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ተነግሮት በኢየሱስ አመነ። እስጢፋኖስ ኢየሱስን በጣም የሚወደው ሰው ሆነ። ሰው ሁሉ ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ እንዴት እንደሞተና እንደተነሳ እንዲያውቅ ለማድረግ ፈለገ። ኢየሱስን የገደሉት ክፉ ሰዎች እስጢፋኖስ ስለኢየሱስ ለሌሎች የተናገረ መሆኑን ሰሙ። በኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች ቁጥር እንዲጨምር ስላልፈለጉ እነኚህ ሰዎች በእስጢፋኖስ ላይ የሀሰት ወሬን አወሩበት። ከከተማ ውጪም ጎትተው ወስደው በድንጋይ ወገሩት። እስኪሞት ድረስም በድንጋይ መውገራቸውን አላቆሙም ነበር። ነገር ግን እግዚ አብሔር በዚህ የመከራ ጊዜ ውስጥ ለእስጢፋኖስ ደስታና ብርታትን ሰጠው። እስጢፋኖስም ቢሞት ወደ ሰማይ በመሄድ ከኢየሱስ ጋር እንደሚሆን አወቀ።



ልጆች! እናንተም ስለኢየሱስ መከራን ልትቀበሉ ትችላላችሁ። ቤተሰቦቻችሁም ወይም ጓደኞቻችሁ ኢየሱስን በማመናችሁ ሊቆጧችሁና ሊቃወሟችሁ ይችላሉ። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ሊስቁባችሁ ወይም ሊሰድቧችሁ ይችላሉ።

ሰይጣን በጌታ ኢየሱስ በማመናችሁ ምክንያት፣ ሌሎች ሰዎች እንዲጠሉዋችሁ በማድረግ ተስፋ እንድትቆርጡና በእግዚአብሔር ላይ እንድትቆጡ ይፈልጋል። ነገር ግን ስለእግዚአብሔር መከራን በምትቀበሉ ጊዜ፣ እርሱ ራሱ መከራውን ለማለፍ እንድትችሉ እንደሚያበረታችሁ ማመን አለባችሁ። እርሱ ድፍረትን ይሰጣችኋል። ልጆች! ችግር በሚደርስባችሁ ጊዜ ለእርሱ ችግሩን እንድትነግሩት፣ እንድ ታመሰግኑት፣ የራሱን ስራ እንዲሰራና እንዲረዳችሁ እርሱን እንድትጠብቁ ይፈልጋል።



ማስታወስ ያለባችሁ ነገር ልጆች! ስለኢየሱስ መከራን የተቀበላችሁት እናንተ ብቻ አለመሆናችሁን ነው። ልክ እንደ እስጢፋኖስ ሁሉ ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ስለ ኢየሱስ መከራን ተቀብለዋል፤ ተገድለዋልም። እነኚህ እግዚአብሔርን የሚወዱ ሰዎች ጌታ ስለእርሱ መከራን እንዲቀበሉ ስለፈቀደላቸው ደስተኞች ነበሩ። ልጆች! ስለእግዚአብሔር መከራን ስትቀበሉ እርሱ ራሱ ደስታን እንዲሰጣችሁና እንዲያበረታችሁ ጠይቁት።

*«... ክርስቲያን በኢየሱስ ያመነ እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር» (1 ጴጥ. 4፥16)*



# ኢየሱስ በቅርቡ ተመልሶ እንደሚመጣ ታውቃላችሁ?

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከሄደ ብዙ ጊዜ የሆነው ይመስላል። ልጆች! «ኢየሱስ ወደ ምድር እመለሳለሁ ብሎ ቃል ኪዳን እንደገባልን መቼ ነው ተመልሶ የሚመጣው?» ብላችሁ ትጠይቃላችሁ? ለመሆኑ ኢየሱስ ወደ ሰማይ የሄደበትን ጊዜ ታስታውሳላችሁ? ለደቀ መዛሙርቱ የመጨረሻ ትእዛዞቹን ከሰጣቸው በኋላ እነርሱ እያዩት ወደ ሰማይ አረገ። በሁኔታው የተገረሙት ደቀ መዛሙርት እንጋጠው ወደ ሰማይ ሲመለከቱ ሁለት መላዕክት መጥተው «ወደላይ የምትመለከቱት ለምንድነው?» ኢየሱስ ልክ ወደ ሰማይ እንደሄደ ሁሉ ተመልሶ ወደ ምድር ይመጣል። እንደገና በደመና ታጅቦ ይመለሳል» አላቸው።

መላዕክት የነገሯቸው ተስፋ ደቀ መዛሙርቱን በጣም አስደሰታቸው። የኢየሱስን መምጣት ሲጠባበቁ ሳለ ጌታ እንዲያደርጉት ያዘዛቸውን ስራ በመስራት መበርታት ጀመሩ።





ልጆች! ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ ብዙ አመታት አልፈዋል፤ እስከ አሁንም ተመልሶ አልመጣም። ነገር ግን ቃል ኪዳን ስለገባልን ተመልሶ እንደሚመጣ እናውቃለን። ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣው መቼ ነው? ማንም ቢሆን ትክክለኛ ጊዜውን አያውቀውም። በጣም በቅርቡ ሊሆን ይችላል። ለመሆኑ ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ ምን ይሆናል? መጽሀፍ ቅዱስ እየሱስ ከመላእክቱ ጋር ድንገት እንደሚመጣ ይናገራል። ያን ጊዜም በምድር ሁሉ የሚሰማ መለከት ይነፋል። ጌታ ኢየሱስን አዳኛቸው አድርገው የሚያምኑም ሁሉ እርሱን ለመቀበል ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ይላሉ። ያኔ በሰማይ ለዘላለም ከኢየሱስ ጋር የምንኖርበትን አዲስ አካል እንለብሳለን።

የኢየሱስን ተመልሶ መምጣት ስንጠብቅ ታዲያ ማድረግ ያለብን ምንድነው? እግዚአብሔርን የበለጠ ለማወቅ መጣር አለብን። ያዘዘንንም በመፈጸም ሌሎች ሰዎችም እንደ እኛ እርሱን እንዲያውቁት ልንረዳቸው ይገባል።

*«ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመለከትም አስቀድሞ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና...» (1 ተሰ. 4፥16)*

ኢየሱስ አንድ ቀን ተመልሶ እንደሚመጣ ቃል ገብቶልናል። ታዲያ ተመልሶ ሲመጣ ከእርሱ ጋር ለመገናኘት ትዘጋጃላችሁ።

ልጆች! ስለእግዚአብሔር ዘወትር ለማወቅና በሕይወታችን ውስጥ ያለውን እቅድ ለመረዳት የሚረዷችሁ ነገሮች ከዚህ በታች አሉላችሁ።

## ዘወትር መጽሀፍ ቅዱስን አንብቡ።

ያለማቋረጥ በመጸለይ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገሩ።

## ትእዛዛቱን ፈጽሙ።

## እርሱን አምልኩት።

ልጆች! እግዚአብሄር ኢየሱስ ክርስቶስን በመስጠት ስላዳናችሁ አመስግኑት። እግዚአብሄርን ምን ያህል እንደምትወዱት ለራሱ ለእግዚአብሄር መንገራችሁን አትርሱ።



## የሚጠኑ የመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች

ልጆች! በሳምንት ቢያንስ አንድ ጥቅስ በቃላችሁ ለመያዝ ሞክሩ።

- «የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማታፍርም ሰራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ» *(2 ጢሞ. 2፥15)*
- «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» *(ፊልጵ. 4፥13)*
- በኃጢአታችን ብንናዘዝ (በእግዚአብሔር ፊት ምህረቱን ለመ ጠየቅ ብንቀርብ) ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመጽም ሁሉ ሊያነጻን (ይቅር ሊለን) የታመነና ጻድቅ ነው» *(1 ዮሐ. 1፥9)*
- «በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና» *(1 ተሰ. 5፥18)*
- እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያቢሎስን ግን ተቃወሙት፤ ከእናንተም ይሸሻል፤» *(ያዕ. 4፥7)*
- «በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ።» *(ፊልጵ. 4፥4)*
- «የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፤» *(ኤፌ. 4፥28)*
- «እኔ (እግዚአብሔር) አልለቅህም ከቶም አልተውህም......» (ዕብ. 13፥5)
- «እርስ በእርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩሆች ሁኑ፤ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ» *(ኤፌ. 4፥32)*

- «ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ! ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፣ የማትነቃነቁም፣ የጌታም ስራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ» *(1 ቆሮ. 15፥58)*

- «እኔ ግን እላችኋለሁ! በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፣ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤...» *(ማቴ. 5፥44)*

- «እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትመጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውንም ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት» *(1 ቆሮ. 10፥31)*

- «በአንተ ላይ ታምናለችና በአንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ» *(ኢሳ. 26፥3)*

- «ስለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው» *(ዮሐ. 1፥12)*

All rights reserved. This book may not be reproduced or translated in part or in total without express permission from CEF Press, Box 348, 17482 Hwy M, Warrenton, MO 63383 USA

Scripture taken from the HOLY BIBLE, NEW INTERNATIONAL VERSION® NIV®. Copyright © 1973,1978,1984 by the International Bible Society. Used by permission of Zondervan Publishing House. All rights reserved.